# የአየር ንብረት ለውጥና የካርቦን ንግድ በኢትዮጵያ

በአቶ ደስአለኝ መስፍን

## 1. አጠቃላይ

የአየር ንብረት ለውጥ በተፈጥሮም አለ። የከባቢ አየርም ባዕድ ነገሮችን ተቀብሎ ጉዳት አልባ የማድረግና የመሸከም አቅም አለው:: ይህም ከአዳዲስ ክስተቶች ጋር እራሱን አላምዶ ለመቀጠል አስችሎታል። ከባዕድ ነገሮች ለሚከተልበት ጉዳት ቅፅበታዊ ምላሽ የመስጠት አቅም ግን የለውም:: ምላሽ ለመስጠት ከሚችልበት ደረጃ እስኪደርስ ጊዜ ይወስዳል። የአሁኑ የአየር ንብረት ለውጥ ግን የተለዩ ነው:: የግሪንሃውስ ጋዞች ወይም የበካይ ጋዝ ልቀት ሙሉ በሙሉ ዛሬውኑ ቢቆም እንኳን የዓለም መሞቅ ይቀጥላል። ምክንያቱም አዝጋሚውን ተፈጥሮአዊ የአየር ንብረት የለውጥ ሂደት የሰው ጣልቃ ገብነት አፋጥኖታል። የአየር ንብረት ለውጥ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ የተጀመረው ደግሞ ችግሩ ከተንሰራፋ በኋላ ነው:: ስለዚህ የጥረቱ ውጤትም የሚታየው ከዓመታት በኋላ ይሆናል። ይህ ደግሞ ትውልድ ተሻጋሪ ተፅዕኖ አስከትሏል።

የበለፀጉ አገሮች በተገበሩት የተሳሳተ የልማት አቅጣጫ የከባቢ አየር ተበክሏል። ከመሸከም አቅሙ በላይ በጨመሩበት በካይ ነገርም የከባቢ አየር ጤናማነቱ ተዛብቷል። ማንም አዳጊ አገር የበለፀጉት ከመበልፀጋቸው በፊት የተከተሉትን ተከትሎ የማደግ ዕድሉ ጠቧል። አዳጊዎች እንደበለፀጉቱ በካይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር እየለቀቅን መልማት አይቻለንም። ምክንያቱም የከባቢ አየር ሥርዓተ መህድር በካይ ነገሮችን ተቀብሎ ጉዳት አልባ የማድረግ አቅሙ ከኢንዱስትሪ አብዮት አንስቶ በተቀበለው የበካይ ጋዝ ምክንያት ተናግቷል። ይህ የአቅም ጉድለት ተጨማሪ በካይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር የሚገባበትን ስፍራ አጥቦታል። ስለዚህ የበለፀጉ አገሮች የፈፀሙትን ታሪካዊ ስህተት የመድገም አዋጪነት ኢምንት ነው::

## 2. የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት የተለያዩ ቡድኖች ስጋት

የነዳጅ ዘይት አምራች አገሮች ስጋት ነዳጅ የከባቢ አየር ብክለት የሚያስከትል በካይ ጋዝ ያመነጫል። በጥቅም ላይ መዋሉ ቢከለከል ወይም ደግሞ ነዳጅን የሚተካ ሌላ የሃይል ምንጭ በስራ ላይ ቢውል ያሰጋቸዋል። ምክንያቱም ለእነሱ ነዳጅ የኢኮኖሚያቸው መሰረት ነው።

የበለፀጉ አገራት ስጋት የበካይ ጋዝ የሚያመነጭ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ የተከለከለ እንደሆነ ነው:: ምክንያቱም ወደ ንፁህ ልማት መቀየር የሚያስከትለው ወጪ ከፍተኛ ስለሚሆን ስራቸውን የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ኢንዱስትሪዎች ስራቸውን ለሚቋረጥ ሊገደዱ ይችላል።

ከአዳጊ አገሮች የመነጨና ለአሁኑ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚሆን የበካይ ጋዝ መጠን ከቁጥር አይገባም። ይልቁንም በተፈጥሮ ሃብት ላይ በቀጥታ ህይወቱ ለተመሰረተው፣ በቂ የመሰረተ ልማት አውታር ለሌለው፣ ደካማ ማህበራዊና የሰው ካፒታል ላለው ስለዚህም የድሃ አገር ህዝብና አካባቢ በአየር ንብረት ለውጥ ይበልጥ ተጎጂ ነው። በአየር ንብረት መዋዥቅ የስርዓተ መህድር አቅም ይደክማል። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተከተለ ድርቅ፣ ጎርፍ እና ሙቀት የውሃ ሃብት፣ ግብርና፣ ደን፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ የሃይል አቅርቦት፣ የሰውና የእንስሳ ጤና፣ ሌሎች ለህይወትና ለብልፅግና የሚያስፈልጉ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የአካባቢ ሃብቶች ይጎዳሉ። ስለዚህ አዳጊ አገሮች ባልፈፀምነው ጥፋት መጎዳት የለብንም። በካይ ጋዝ የሚያመነጩቱ ስህተታቸውን ማረም አለባቸው። የሌሎችን በካይ ለመምጣጥ ብለን ደግሞ ድህነትን

---

አቶ ደሳለኝ መስፍን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሕግ ሙያ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአካባቢ ጥበቃና ልማት አግኝተዋል። አቶ ደሳለኝ መስፍን በአሁኑ ሰዓት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ም/ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ ኢትዮጵያን ወክለው በተለያዩ አለም አቀፍ ኮሚቴዎች ውስጥ በሰብሳቢነትና በአባልነት አገልግለዋል በማገልገልም ላይ ይገኛሉ። አቶ ደሳለኝ መስፍን በአካባቢ ጥበቃና ልማት ዙሪያ በርካታ ጹሑፎችን የጻፉና ያቀረቡ ናቸው።

ለማጥፋትና ለመልማት የምናካሂደውን እንቅስቃሴ መግታት አይጠበቅንም ይላሉ። ከአዳጊ አገሮች መካከል ትናንሽ ደሴቶችን የባህር ከፍታ በመጨመሩ ሊሰምጡ ይችላሉ። እንደ ዓለም ባንክ ግምት የባህር ከፍታ በ 1 ሜትር ቢያድግ 56 ሚሊዮን ህዝብ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናል። ስለዚህ የእነርሱ ጥያቄ የመኖራቸውን ቀጣይነት ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው። የስካንዲኔቪያን አገሮችና አውሮ□ውያን ደግሞ የአዳጊ አገሮችንና የትናንሽ ደሴቶችን ስጋት ይጋራሉ። የአየር ንብረት ለውጡ እንዲስተካከልም የማያወላውል አቋም አሏቸው። የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት የተካሄደውም ድርድር እነዚህን ቡድኖች ያካተተ ነበር።

### 3. የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ኮንቬንሽን

የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንቬንሽን በ1992 ወጥቷል። ይህ ኮንቬንሽን በባህሪይው ማዕቀፋዊ ነው። ከፖሊሲ ሰነድ እምብዛም አይለይም። የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን እንዲቀነስ ከማመቻቸት ያለፈ ይዘት የለውም። በኮንቬንሽኑ ድንጋጌ መሰረት የከባቢ አየርን ደህንነት መጠበቅ የጋራ ጉዳይ ነው። የከባቢ አየር ጠ ͅናማ ተስተጋብሮት መዛነፍም የጋራ ችግር ነው። ቀዳሚ ሃላፊነቱም የከባቢ አየር በካይ አገሮች ነው። የአየር ንብረት ለውጥ በድንበር አይከለልም። በሁሉም አገሮች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል። የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር የባህርን ጠ ለል፣ የበረዶን ክምችትና የዝናብን ወቅት የሚመለከቱ ሁኔታዎች ማናጋቱ ግልፅ ሆኗል። የከባቢ አየር በካይ ልቀት ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ዝቅ ካላለ የውሃ አቅርቦት ይቀንሳል፣ የምግብ እጥረት ይከተላል። የህይወታዊ ሃብቶች ለጥፋት ይዳርጋሉ። የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን ስደተኛ ያደርጋል፣ ለህልፈትም ይዳርጋል። የአየር ንብረት ለውጥን ማቆም ከአቅም በላይ ሆኗል። ስለዚህ ለውጥን መላመድ ለማንም አገርና ሕዝብ አስፈላጊ ነው። በበለፀጉት አገሮች ዘንድ ግን ለውጡን ለመመከት የሚያስችል የተቋም፣ የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅም ደርጅቷል። አቅሙ የጎደለው ከአዳጊ አገሮች ዘንድ ነው። የሚገነባው ደግሞ ድህነትን በአካባቢ እንክብካቤ ላይ በተመሰረተ ልማት በማጥፋት ነው። ይህ ድህነትን የማጥፋት ጥረት ቁጥሩ እያደገ ያለውን የህዝብ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት በ2030 ዓ.ም የዓለም ከባቢ አየር ሙቀትን ለማስተካከል ከሚካሄደው ጥረት ጋር የተገናዘበ ልማት በአዳጊ አገሮች ለማካሄድ ከ200 እስከ 210 ቢሊዮን ዶላር መመደብ አለበት። ለአዳጊ አገሮች የአየር ንብረት ለውጥ የመልመጃ አቅም መገንቢያ ከ28 እስከ 67 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። እንደ አክስፋም ግምት ከሆነ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን ለመላመድ አዳጊ አገሮች 50 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ መመደብ አለባቸው። ይህን ወጪ የመሸፈኑ ሃላፊነት የበለፀጉት አገሮች ነው።

### 4. ከአየር ንብረት ለውጥ በአገራችን የሚከተሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች

ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ባንሆንም ለውጡን የሚያስከትሉ በካይ ጋዞችን የሚያመነጩ አገሮች እርምጃ እንዲወስዱ የሞራል ግፊት ማድረግ አገራዊ አቋማችን ስለመሆኑ በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ተብራርቷል። ከአየር መዛባት የተከተለ ድርቅ በተደጋጋሚ ጥቃት አድርሶብናል። በዚሁ ምክንያት በብዙ ሺህ የሚቆጠ ሩ ወገኖቻችን ተርበዋል፣ ሞተዋል። ወንዞቻችንም ሆኑ የዕፅዋት ሽፋኖች በዚሁ ችግር ተጠቅተዋል። ወንዞቻችን በመጠን እየቀነሱም ብቻ ሳይሆን የምንጮች መድረቅም ተከስቷል። በአጠቃላዩ በገንዘብ አስልቼ ማሳየት ባልችልም በኢትዮጲያ ላይ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው።

#### 4.1.በግብርናው መስክ፣

ተደጋጋሚ የወቅት መዛባት፣ የአየር ሙቀት መጨመርና የክስተቱ መራዘም በግብርና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል። የክረምትና የመኸር ወቅት መግቢያና መውጫ ሲቀያየር ምርት ይቀንሳል። ይህንኑ ተከትሎ ድርቅ ይከሰታል። የተከተለን ጉዳት እንደነበር ለመመለስ ወይም ተፅዕኖውን ለማቃለል ደግሞ ሃብት ይጠ ይቃል። ይህ ደግሞ ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ፣ ለውሃ አቅርቦት የመሳሰሉ ተግባራት የተመደበውን

ስለሚያስቀንስ የአገር ሃብት ድንገት ለመጣ አደጋ ማስተካከያ ይውላል።

4.2. በኢንዱስትሪው መስክ፣
የአየር ንብረት ለውጥ ለምሳሌ፣ በውሃ ሃብት ላይ በሚያስከትለው ጉዳት የሃይል ማመንጫዎች አቅም ይዳከማል። የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም በመዳከሙ የሚከተለው መናጋት ከዕለት ጉርስ እጥረት እስከ ድርጅት መዘጋት ይዘልቃል። ውሃን በብዛት የሚጠ ቀሙ ፋብሪካዎች፣ ለምሳሌ የጨርቃ ጨርቅንና የቆዳ ፋብሪካን የመሰሉት በሰው ጉልበት በስፋት ይጠቀማሉ። በተባሉት ፋብሪካዎች ዘንድ የውሃ እጥረት ከተከተለ አትራፊነታቸው ይናጋል። ሰራተኛም ይቀንሳል። ይህ ደግሞ ሥራ የመፍጠር ጥረትንና የአገር ውስጥ የገቢን መሰረት ያሳንሳል።

4.3.የበሽታ አምጪ ተህዋሲያን መብዛት፣
የአየር መዛባት ለንዳድ ወይም ለወባ ትንኝ የመፀናወት አቅም ይፈጥራል፡፡፡ የሙቀት መጨመር ለበሽታ አምጪ ተህዋስያን ምቹ የመራቢያ ሁኔታ ያበጃል። የበሽታ አዛማቾች መፈልፈልም ሆነ ዕድሜ በሙቀትና በወበቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ተላላፊ ወረርሽኞች የሚገኑትም ሆነ የሚደክሙት እንደ ወቅቱ ምቹ መሆን ወይም ያለመሆን ነው። ከጎርፍ በሚከተል የውሃ መበከል ህዝብን ለውሃ ወለድ በሽታ ይዳረጋል። በዚህ ክስተት ጠ ንነቱ የተጎዳ የማምረት አቅሙ ይገደባል። የጤናን ቀውስ ለማከም የሚወጣ ወጪ ደግሞ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በአገር ደረጃ ጥሪት የማካበት አቅምን ይጎዳል።

4.4. የግጦሽ መሬት መጎሳቆል፣
ከብት አርቢው ማህበረሰብ ለእንስሳቱ ሳርና ውሃ ለማቅረብ እንዲያስችለው ከአንድ ስፋራ ወደ ሌላ ይዘዋወራል። የዝውውሩ መሰረት ትቶት የሄደው ሥፍራ አገግሞ ይቆየኛል ብሎ ነው። በወቅት መዛባት ምክንያት ያገግማል የተባለው የግጦሽ መሬት ሳያገግም ሲቀር ሰውም እንስሳቱም ከአደጋ ይወድቃሉ። የዚህ ችግር ውጤት በመኖ አቅርቦት አይወሰንም። የእንስሳት ሃብቱን ለጥፋት ያጋልጣል። የእንስሳ የገበያ ዋጋ ይዛነፋል። የዋጋ መዛነፉም ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል። በውስን የተፈጥሮ ሃብት ላይ ሽሚያ ከተፈጠረ ማህበራዊ ቀውስ ሊከተል ይችላል።

4.5.የሰው ጤናና የአደጋ ተጋላጭነት፣
ጎርፍ የውሃ ማስተላለፊያ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ወይም ሌላ የመሰረተ ልማት አውታር ያበላሻል። በጎርፍ የታጠበ ጎጂ ኬሚካልም ሆነ ሌላ በሽታ አምጪ፣ ለምሳሌ ከቆሻሻ ማከማቻ ስፍራ ወይም ማስወገጃ ስፍራ በቀጥታ በዚሁ ገብቶ በህዝብ ጤና ላይ አደጋ ያስከትላል። በድርቅ ወይም በጎርፍ ምክንያት ቤት የፈረሰባቸው መልሰው እስኪቋቋሙ በአንድ መጠለያ ተፋፍገው ይሰፍራሉ። ሰውም፣ እንስሳቱም ሆኑ ሌሎች እንቅስቃሴዎች በውስን የውሃ ምንጭ ሲያተኩሩ የውሃ ምንጩ ለብክለትና ለውሃ ወለድ በሽታ ይጋለጣል። በሌላ በኩል የአንድ ወቅት ተጋላጭነት ሳይስተካከል ሌላ የመጋለጥ አደጋ ሊከተል ይችላል። በዚህ ክስተት ከመጀመሪያው ይልቅ ከሚቀጥለው ተጋላጭነት የሚከተል ጉዳት ይብሳል። በጎርፍ ቤቱ የፈረሰበት ሰው አማራጭ በመጥፋቱ ወይም በአቅም ዕጦት ከዚያው ስፍራ ቤቱን ጠግኖ መኖር ከቀጠለና ተመሳሳይ ጎርፍ ከተከሰተ፣ ተጋላጩ ከመጀመሪያው ይልቅ በቀጣዩ ክስተት የበለጠ ይጎዳል።

4.6. የተፈጥሮ ሃብቶች በጎ ሁኔታ መጎሳቆል፣
በአየር መዛባት በሚከተል ጎርፍና ነፋስ አፈር ይከላል። ለምነቱም ይቀረቀዝና ጠቃሚ አገልግሎት የማበርከት አቅሙ ይደክማል። ይህ ይበልጥ ጉዳይ የሚያስከትለው ለበረሃማነት በተጋለጡ የአገራችን መሬቶች ላይ ነው። በኢትዮጵያ የእነዚህ መሬቶች ስርጭት ሰፊ ነው። በዝናብ ወቅት መዛባት የውሃ እጥረት ይከተላል። የውሃ ውስጥ ህይወታዊ ሃብትም በመጠንና በጥራት ያሽቆለቁላል። ለምሳሌ ውሃ ሲቀንስ የዓሳ ሃብት ከአደጋ ላይ ይወድቃል። ይህ ደግሞ ርካሽ የፕሮቲን ምንጭ የሆነውንና አብላጫው ህዝብ እራሱ አስግሮ ወይም በቀላል ወጪ የሚያገኘውን የምግብ ምንጩን ያሳጣዋል። የአየር ንብረት የበለጠ የሚያጠቃው በቀላሉ የሚጎዳ መሬትን ነው። በዝናብ ወቅት መዛባት ወይም በሙቀት መጨመር በሚከተል ትነት በውሃ አዘል መሬት ላይ የውሃ እጥረት ሊከተል ይችላል። የውሃ አዘል መሬት መጎሳቆል የቤት ክዳን ሳር፣ በበጋ ወቅት የከብት መኖ መገኛ፣ የአዕዋፍ መራቢያ ወይም መቆያ ስፍራን፣ የቱሪስት መስህብን ጭምር ይጎዳል።

የዕፀዋት ሽፋን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ በህይወታዊ ሃብት ላይ የሚያስከትለውን ዓይነት ጉዳት የህይወታዊ ሃብትም ጥፋት የአየር ንብረትን ያዛባል፡፡ በአካባቢ አደጋ የእንስሳትና የዕፅዋት መኖሪያ ይጎሳቆላል፡፡ በጎርፍና በሙቀት ሰውም ሆነ እንስሳ ካሉበት ስፍራ ይሰደዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ካሉበት ሥፍራ ቢቆዩም ቁጥራቸው ይቀንሳል፡፡ በተራራማ ሥፍራ ላይ ያሉት ግን የሚሰደዱበት ተስማሚ ስፍራ ማግኘታቸው አጠራጣሪ ነው፡፡

## 5. የንፁህ የልማት ዘዴ /CLEAN DEVELOPMENT MECHANISM/

የበለፀጉ አገሮች በ2000 የበካይ ልቀታቸውን 1990 ወደ ነበረው የልቀት ልክ ዝቅ እንዲያደርጉ ኮንቬንሽኑ ደነገገ፡፡ ይህ ድንጋጌ ውጤት ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በኪዮቶ ፕሮቶኮል በግዴታ የሚሰራበት የልቀት ማስቀነሻ ድንጋጌ ወጣ፡፡ የኪዮቶ ፕሮቶኮል በ2005 ዓ.ም ፀደቀ፡፡ ፕሮቶኮሉ የበለፀጉ አገሮችን ኃላፊነት ይደነግጋል፡፡ ታዳጊ አገሮችም የከባቢ አየር በካይ ጋዝ ልቀት የማያመነጭ ልማት እንዲከተሉ ያበረታታል፡፡ በዚህም መሰረት ከ2008 እስከ 2012 ባሉት ጊዚያት የበለፀጉ አገሮች 1990 ከነበረው የልቀታቸው ልክ ላይ በአማካይ 5 በመቶ እንዲቀንሱ ፕሮቶኮሉ ደንግጓል፡፡ ይህንንም ድንጋጌ ለማስፈፀም 3 ዘዴዎች በፕሮቶኮሉ ተካተዋል፡፡ እነዚህም የልቀት ንግድ፣ የጋራ ትግበራ እና ንፁህ የልማት ዘዴ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ በካይ ኩባንያዎች ልቀታቸውን ባአነስተኛ ወጪ እንዲቀንሱ እነዚህ ዘዴዎች ያግዟቸዋል፡፡ የጋራ ትግበራ እና የንፁህ የልማት ዘዴ የሚተገበሩት በቅድሚያ ፕሮጀክት ተዘጋጅቶ ነው፡፡ የጋራ ትግበራ የመልከዓ ምድር የተፈፃሚነት ወሰኑ በምስራቅ አውሮጳና በሩሲያ ምድር ነው፡፡ የንፁህ የልማት ዘዴ ደግሞ በአዳጊ አገሮች ዘንድ ነው፡፡

### 5.1. የንፁህ የልማት ዘዴ ተቋማዊ አጠቃላይ ሁኔታ፣

በሰባተኛው የኮንቬንሽኑ አባል አገራት በፀደቀው የማራክሽ አኮርድ የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ተፈላጊ ሁኔታዎች ተዘርዝረዋል፡፡ የፕሮጀክቶቹን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ገለልተኛ አካልም ተሰይሟል፡፡ ይህም ዴዚግኔትድ ኦፐሬሺናል ኤንቲቲ እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህ አካል ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው ፕሮጀክት እንዲፀድቅ የውሳኔ ሃሳቡን በአባል አገራቱ ለተቋቋመው ኤክሲኪዩቲቭ ቦርድ ያቀርባል፡፡ በቀረበው ሃሳብ ላይ ቦርዱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የንፁህ የልማት ዘዴ በገበያ ስርዓት ይመራል፡፡ የሰብዓዊ ዕርዳታ አካል አይደለም፡፡ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ውድድር አለበት፡፡ ስለዚህ በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶች ዝግጅትና ትግበራ የተለያዩ ስጋቶች አሉ፡፡ የተዘጋጀ ፕሮጀክት ሊፀድቅም ላይፀድቅም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፤ በብሔራዊ ደረጃ ከሚመለከተው አካል በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ ተቃውም የሌለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ላይሰጥ ይችላል፡፡ በመረጃ እጥረት ምክንያት የኤክዚክዩቲቭ ቦርዱ ፕሮጀክቱን ላያፀድቀው ይችላል፡፡ ፕሮጀክቱ ሲገመገም ከነአካቴውም ሊወድቅ ይችላል፡፡ በክትትልና ግምገማ ወቅት በመጀመሪያ ተሰልቶ የነበረው የካርቦን ክሬዲት መጠን ዝቅ ሊል ይችላል፡፡

### 5.2. የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የዝግጅት ሂደት አጠቃላይ ሁኔታ፣

አንድ የበለፀገ አገር ኩባንያ ወይም መንግሥት የበካይ ጋዝ ልቀቱን ለማካካስ በአዳጊ አገር የሚተገበር ፕሮጀክት ከመንግሥት፣ ከግል ወይም ህጋዊ ዕውቅና ካላቸው ማህበረሰቦች ሊገዛ ይስማማል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ባይኖርና የተለመደው አሰራር ቢቀጥል ሊከተል የሚችለው የከባቢ አየር በካይ ልቀት መጠን ይሰላል፡፡ የበለፀገው አገር ኩባንያ ወይም መንግሥት ይህንኑ የልቀት መጠን ይገዛል፡፡ ይህም ወደ ከባቢ አየር እንዳይገባ ወይም ደግሞ ከከባቢ አየር ተመጥጦ የተቀነስ የበካይ ጋዝ መጠን ለገዢው ብክለቱን እንደቀነሰ ተቆጥሮ ይመዘገብለታል፡፡ ለምሳሌ አንድ የአሜሪካ ኩባንያ አሜሪካ እንድትቀንስ የሚጠበቅባትን የልቀት መጠን ለማሟላት ይፈልጋል፡፡ ይህም ኩባንያ እዚያው በአገሩ እያካሄደ ባለው ፋብሪካ ውስጥ ቴክኖሎጂ ጨምሮ ወይም የአሰራር ዘዴውን አሻሽሎ የሚለቀውን በካይ ለመቀነስ አልተቻለውም፡፡

በኢትዮጵያ ዘንድ ደግሞ ከህይወታዊ ሃብት ነዳጅ የሚያለማ ፋብሪካ እንዲተከል ሃሳብ ቢኖርም በገንዘብ ዕጥረት ምክንያት ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም፡፡

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ፋብሪካዎች የከባቢ አየር በሚበክል የድንጋይ ከሰል ለመጠቀም ተገደዋል፡፡ ፋብሪካው በኢትዮጵያ ቢተከል የድንጋይ ከሰልን መሰረት ያደረገ የኢትዮጵያ ፋብሪካ በንፁህ የሃይል ምንጭ መጠቀም ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ከኢትዮጵያ መንጭቶ የከባቢ አየር ብክለትን የሚያባብስ ልቀት ይወገዳል፡፡ ይህም የተወገደው መጠን ተሰልቶ ለአሜሪካው ኩባንያ ይሸጥለታል፡፡ በገንዘቡም የታቀደው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ምድር ሊተገበር ይችላል፡፡ ለአሜሪካ ደግሞ ይህ አስተዋፅዖ በአገሯ ከሚለቀቀው የበካይ ልቀት መጠን ላይ ይቀነስላታል፡፡

## 5.3. የፕሮጀክት ዲዛይን ዶክዩመንት ዝግጅት

የፕሮጀክት ዲዛይን ዶክዩመንት በሻጩ መዘጋጀት አለበት፡፡ በፕሮጀክቱ ላይ የሻጭ አገር ሕግ በሚፈቅደው መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መካሄድ አለበት፡፡ ይህ ሰነድ ማብራራት ከሚጠበቅበት ጉዳዮች አንዱ ፕሮጀክቱ ባይኖርና የተለመደው አሰራር ቢቀጥል የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን ምን ይሆን ነበር የሚለውን ነው፡፡ በዚህም መልክ ፕሮጀክቱ ያካካሰው የበካይ ጋዝ ልቀት ተሰልቶ ይሸጣል፡፡ ከፕሮጀክቱ ትግበራ በፊት የነበረውን ሁኔታ የሚገለፀው እንዲሁም በፀደቀ ፕሮጀክት ላይ ክትትልና ግምገማ የሚካሄደው የኤክሲክዩቲቭ ቦርደ ባፀደቀው የአሰራር ዘዴ መሰረት ነው፡፡ ይህም ቢሆን ሌላ የአሰራር ዘዴ ባለፕሮጀክቱ ማዘጋጀት ይችላል፡፡ ተቀባይነት የሚኖረው ግን የተባለው የአሰራር ዘዴ በኤክዝኪዩቲቭ ቦርድ ተገምግሞ ከፀደቀ ነው፡፡

## 5.4. የተሳታፊ አገሮች ማረጋገጫ

በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ተሳትፎ በውዴታ ስለመሆኑ የሻጭና የገዢ አገሮች የሚመለከታቸው አካላት ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው፡፡ የሻጭ አገር መንግሥት ግን ፕሮጀክቱ የአገሩን የዘላቂ ልማት ዕቅድና ጥረት እንደሚያራምድ የፅሁፍ ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡ ፕሮጀክቱ በኮንቬንሽኑ ድረ ገፅ ላይ ወጥቶ አስተያየት ይሰባሰባል፡፡ የፕሮጀክት ሰነዱን ይዘትና በፕሮጀክቱ ይዘት ላይ የተሰጠ የሕዝብ አስተያየት በማገናዘብ አፅዳቂው አካል ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ፕሮጅክቱ ተቀባይነት ካገኘ በኤክዚኪዩቲቭ ቦርድ ይመዘገባል፡፡ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀትም ለፕሮጀክቱ ባለቤቶች ይሰጣል፡፡ የተቀነሰው የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንም ይፋ ይሆናል፡፡

# 6. የንፁህ የልማት ዘዴ ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ

በአገራችን ከንፁህ የልማት ዘዴ ሊጠቀሙ የሚችሉ ፋብሪካዎች፣ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የእርሻ ልማቶች፣ በደህና ሁኔታ ላይ ያሉ ደኖች፣ የተጎሳቆሉ የደን መሬቶች፣ እንክብካቤ የሚሹ ጥብቅ ስፍራዎችና የዕፀዋት ሽፋናቸውን የተገፈፉ ባዶ መሬቶች አሉ፡፡ ከሕይወታዊ ሃብት የሃይል ፍላጎትን የሚያሟላ ነዳጅም በአገር ውስጥ ሊመረት ይችላል፡፡ይህም በየወቅቱ ዋጋው የሚጨምረውን በካዩ ነዳጅ የሚያስከትልብንን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሊያስቀርልን ይችላል፡፡ ከከተማ ቆሻሻ የኤሌክትሪክ ሃይልን አመንጭቶ ማከፋፈል ይቻላል፡፡ የኬሚካል ማዳበሪያ የፔትሮኬሚካል ውጤት ስለሆነ እንደ ፔትሮሊየሙ ዋጋው ያሻቅባል፡፡ በኬሚካሉ ምትክ በተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም ደግሞ የከባቢ አየር ብክለትን ብቻ ሳይሆን ለአገራችን አርሶ አደር ወጪ ይቀንሳል፡፡ በንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት አማካኝነት ይህ አስተዋፅዖ ለካርቦን ንግድ ቢቀርብ ለአገራችን አዲስ የገንዘብ ምንጭ ይሆንልናል፡፡ የጂኦተርማልን ጨምሮ የሃይል ፍላጎትን ከንፁህ የሃይል ምንጭ ለሟሟላት የሚያስችል የአነስተኛ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ፣ የፀሃይ እና የንፋስ ሃብቶች አሉን፡፡ እነዚህን ሃብቶች ግን ማልማትና የአገራችንን የሃይል ምንጭ ሥብጥር ለማብዛት አልቻልንም፡፡ አሁንም የሃይል ፍላጎታችንን በባህላዊ መንገድ እያሟላን ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ሃብቶች ለማልማት ያለን ጥሪት አነስተኛ ነው፡፡

በሌላ በኩል በኪዮቶ ፕሮቶኮል ድንጋጌ መሰረት የከባቢ አየር በካይን ለመቀነስ ታቅዶ እየተተገበረ ያለው ንፁህ የልማት ዘዴ እነዚህን ሃብቶቻችንን ለማልማት በገንዘብ ምንጭነት ሊያገለግለን ይችላል፡፡ የንፁህ የልማት ዘዴ ላይ የተመሰረተ ንግድ እየጎለበተ ነው፡፡ እስከ 2012 ድረስ 2 ቢሊዮን ቶን የበካይ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ተመዝግበዋል፡፡ ለንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ማስተግበሪያ በአጠቃላዩ 11 ቢሊዮን ዶላር ተመድቧል፡፡

እስከ አሁን ያሉት የንፁህ ልማት ዘዴ ፕሮጃክቶች በቻይና፣ በሕንድ፣ በብራዚል፣ በኮርያና በሜክሲኮ ተከማችተዋል። እነዚህ አገሮች እስከ 2012 ድረስ ከሚሸጠው 84 በመቶውን ወስደውታል። በዓለም ላይ ለሺያጭ ከቀረቡት ፕሮጀክቶች መካከል 79 በመቶው የቻይና፣ የሕንድ፣ የብራዚል፣ የኮርያና የሜክሲኮ ነው። በአገራችን በኪዮቶ ፕሮቶኮል መሰረት ለሚካሄደው ንግድ የሚውል ሃብት ቢኖርም ተሳትፎአችን ስለዚህም ተጠ ቃሚነታችን ይህን ያህል አይደለም። እስከአሁን በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ አንዳንድ ዕንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ግን መጠናከር አለባቸው። ስለዚህም ይህ የካርቦን ንግድ በአገራችን እንዳይስፋፋ መሰናክል የሆኑ ጉዳዮችን ለማወቅ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች፣

- ከዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን አንስቶ፣ በሁሉም መስክ ለካርቦን ንግድ የሚውል አገራዊ አቅም የሚያሳይ ስለዚህም የካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንትን የሚስብ ዝርዝር መረጃ አመንጭቶ ለንግዱ ተሳታፊዎች እንዴት ማሳወቅ ይቻላል?

- ንፁህ የሃይል ምንጭ ስብጥርን የሚያስፋፋ እንዲሁም በምግብ ራስን ከመቻል ያለፈ የዘላቂ ልማት የማከሄጃ ጥሪት ለማካበትና ቴክኖሎጂ ለማግኘት የሚያስችል የካርቦን ንግድ በአገራችን እንዲሰፍን ምን ማድረግ እንችላለን?

- የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖ መቋቋሚያና የክስተቱን መልመጃ አገራዊ አቅማችንን በሁሉም ደረጃ በካርቦን ንግድ አማካኝነት ለመገንባት የሚያስችል አዲስና ተጨማሪ የገንዘብ ምንጭ ለማግኘት የሚረዱ ፕሮ ጀክቶች ወጪ ለመሸፈን ምን መደረግ አለበት?

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ለሚካሄድ ውይይት በመነሻነት እንዲያግዝ በማሰብ የሚከተሉት ሃሳቦች ቀርበዋል፣

## 6.1. የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶች ማስፋፊያ ህግ በሚመለከት፣

አሁን ያለን የኢንቨስትመንት ህግ አጠቃላይ ነው። ስለዚህ የንፁህ የልማት ዘዴ ኢንቨስትመንትን የሚሰብ ተጨማሪ የሕግ ሥርዓት ያስፈልጋል። ይህ ህግ የተረጋጋና ሊተገበር የሚችል መሆን አለበት። ምክንያቱም የካርቦን ክሬዲቱ በ10 ዓመታት ለሚቆጠር ጊዜ ይቆያል። ስለዚህ በ10 ዓመታት በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ህግ ሊለዋወጥ ይችላል። ይህ ደግሞ በነባር ህግ ላይ ተመስርቶ ለረዢም ጊዜ ለሚቆይ ኢንቨስትመንት አዋጪ አይደለም። ያለ ህግ ደግሞ የኢንቨስትመንት ዋስትና ላይፈጥር ይችላል።

## 6.2. የካርቦን ንግድ ላይ የተሳትፎ ወሰን በሚመለከት፣

አንዳንድ መሰናክሎች በቀላሉ ሊስተካከሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ማንም ሊረዳው በሚችል መንገድ የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት መገምገሚያና ማፅደቂያ ሥርዓት ማውጣት ቀለል ያለ ነው። በየቱኛው የልቀት መስክ እስከ ምን ደረጃ ድረስ የውጭ ኢንቨስተር ይሳተፍ የሚለውን ዓይነት ጉዳይ ለመወሰን ግን ጊዜ ወስዶ ማሰብ ይጠይቃል። ምክንያቱም ፀድቆ በሥራ ላይ ያለ ህግን ይዘት እንዲሻሻል ወይም እንዲሻር ሊያደርግ ስለሚችል ነው። ለምሳሌ የግል ባለሃብት የኤሌክትሪክ ሃይል አመንጭቶና በማከፋፊያ መስፈር አስገብቶ ቢያሰራጭ የሃይል አቅርቦት ይሻሻላል። ይህ የስራ መስክ የግል ሲሆን ግን ድጎማ ይቀራል። ይህ ደግሞ በኤሌክትሪክ ሃይል የመሸጫ ዋጋ እንዲንር ያደርጋል። የአገር ሕዝብ በኤሌክትሪክ የመጠቀሙ አቅም አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም አብላጫው ህዝብ የሃይል ፍላጎቱን በኩበትና በእንጨት ለማሟላት ይገደዳል።

አንዳንድ አገሮች የውጭ ኢንቨስተር ተሳትፎን ይገድባሉ። ህንድ ዕፀዋት የመትከል ፕሮጀክትን ለውጭ ዜጋ አትፈቅድም። አንዳንድ አገሮች ደግሞ ለካርቦን ፕሮጀክቱ መተግበሪያ የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ በአገራቸው ካለ ኢንቨስተሩ ከአገር ውጭ እንዲያመጣ አይፈቅዱም። እነዚህ ተመክሮዎች በጅምላው ጥሩ ወይም መጥፎ አይባሉም። ሁሉም እንደየአገሩሁኔታ ይለያያል። ስለዚህ ከዚህ ዓይነቱ ተመክሮ ለእኛ ለአብነት የሚሆን ምን ጉዳይ ማግኘት እንችላለን?

### 6.3. የኢንቨስትመንት ወጪ መሸፈኛ ገንዘብ ዕጥረት በሚመለከት፣

አብዛኛውን የካርቦን ክሬዲት የሚገዙት በበለፀገው አገር ያሉ በካይ ኩባንያዎች ናቸው:: በበለፀጉ አገሮች የስራ ፈቃድ ያላቸው 22 ኩባንያዎች ከአዳጊ አገሮች ለካርቦን ክሬዲት መግዣ 160 ቢሊዮን ዶላር ድረስ መድበዋል:: በቢሊዮን የተመደበው ይህ ገንዘብ የካርቦን ክሬዲት ለመግዛት እንጂ የካርቦን ፕሮጀክትን ለሽያጭ እንዲደርስ የማድረጊያ ወጪ ለመሸፈን አይደለም:: የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የሚያልፍበት እያንዳንዱ ሂደት ደግሞ ወጪ ያስከትላል:: የየፕሮጀክቱም ወጪ የተለያዬ ነው:: ከ28 000 እስከ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ ይችላል::

የፕሮጀክት ማዘጋጀና ፕሮጀክቱን ለሺያጭ ደረጃ ለማድረስ የሚያስፈልግ ወጪ በቅድሚያ መሸፈን አለበት:: የካርቦን ክሬዲቱ ወይም የሺያጩ ገንዘብ የሚገኘው ደግሞ በመጨረሻ ነው:: ስለዚህ የአገር ውስጥ ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በራሳቸው ወይም ከዓለም ዓቀፍ መሰል የገንዘብ ተቋማት ጋር በመሆን ለፕሮጀክቶች የመድህን የዋስትና ሽፋን ሊሰጡ ይችላሉ:: ለኢንቨስትመንት የሚውል ብድር ሊያበድሩ ይችላሉ:: ስለዚህም የንግድ አድማሳቸው ስለሚሰፋ እነርሱም ቢሆን ተጠቃሚ ይሆናሉ:: ይህን ማድረጉን እንዲወዱትና የወደዱትንም እንዲፈፅሙት ግን ምን ማድረግ እንችላለን?

### 6.4. የተሟላ የኢንቨስትመንት አቅም መረጃ አመንጭቶ ማሰራጨት፣

ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ተወዳደሪ ፕሮጀክቶችን መለየትና ለአልሚው ማሳወቅ አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ ከነፋስ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ገንብቶ፣ የማስተላለፊያ መስመር ዘርግቶ ያመነጨውን የኤሌክትሪክ ሃይል ለመሸጥ የሚችል የፕሮጀክት ባለቤት ከኤሌክትሪክ ሺያጭ እንዲሁም ከካርቦን ክሬደቱ የዳጎሰ ገቢ ያገኛል:: አሁን ተገንብቶ ያለ በካይ ፋብሪካን አካባቢያዊ ተቀባይነት ወደለው አሰራር ለማሸጋገር የሚካሄድ ፕሮጀክት ደግሞ ገቢው አነስተኛ ነው:: ምክንያቱም የገቢው ምንጭ የካርቦን ክሬዲት ከሚያስገኘው ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ:: እንዲህ ዓይነቱን ጨምሮ፤ በአገራችን ውስጥ የካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንት ዕድል ለማሳየት በአሃዝና በምስል የተደገፈ መረጃ ቢኖር አስፈላጊ ነው:: ይህን መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት እየተካሄደ ባለው ጥረት ውስጥ የሲቪል ማህበራት እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?

### 6.5. የኢኮኖሚያዊ የማበረታቻ እርምጃ በሚመለከት፣

የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክትን ለማስተግበር ወደ አገር የሚገባን ቴክኖሎጂ ከቀረጥ ነፃ ማድረግ ሊታይ የሚገባው አማራጭ ነው:: ከካርቦን ክሬዲት ንግድ ላይ ቀረጥ ማስከፈል ኢንቨስትመንት ሊስብ ወይም ሊያርቅ ይችላል:: ለምሳሌ የካርቦን ክሬዲት ዋጋ በህግ ይወሰን ወይስ ለገበያ ይተው የሚል ጉዳይ አነጋጋሪና በሁሉም አቅጣጫ መታዬት ያለበት ነው:: የበካይ ሃይል ምንጭ ድጎማ ንፁህ የሃይል ምንጭ ልማትንና ስርጭትን ያዳክማል:: በሌላ በኩል፤ ለምሳሌ በደቡብ አፍሪቃ አንዳንድ የከተማ አስተዳደሮች የሃይል ማመንጫ ባለቤት ናቸው:: ስለዚህ ሃይል አመንጭተው በማከፋፈል ገቢ ያገኛሉ:: መስኩን በብቸኝነት ይዘውታል:: የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመራቸው ውስጥ በሌላ አካል የመነጨ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲሰራጭ አይፈቅዱም:: ከህይወታዊ ሃብት የመነጨ ነዳጅም በነዳጅ ማደያ ተጨምሮ እንዲሰራጭ የማይፈልጉ የነዳጅ ማደያ ባለቤቶች ይኖራሉ:: ስለዚህ የሃይል ማሰራጫ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሞኖፖሊ አጠቃቀምን መርምሮ በማሻሻል ጭምር ለካርቦን ንግድ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ እንዴት መፍጠር ይቻላል?

### 6.6. ግንዛቤ ማስፋፋት

በአንድአንድ አገሮች የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክቶችን መርምሮ የማፅደቅ ሂደት አዝጋሚ ነው:: የተለያዩ ባለድሻዎች ተሳትፎም ይህን ያህል አይደለም:: የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት ለልማት የሚያበረክተው አስተዋፅዖን በሚመለከት የባለድርሻዎች ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል:: ስለዚህ ለተለያዩ ባለድርሻዎች ሁለት የተለያዩ ነገር ግን ተደጋጋፊ የሆኑ የግንዛቤና የክህሎት ማጎልበቻ ዕርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው:: የመጀመሪያው የግንዛቤ ማጎልበቻ ዕርምጃ የንፁህ የልማት ዘዴ

የኢንቨስትመንት ዘርፍ ትርፍ የሚያስገኝ መሆኑን ማስገንዘብ ነው:: የሁለተኛው ደግሞ እያንዳንዱ ባለድርሻ ከየድርሻቸው አኳያ የተገናዘበ ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው:: ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤና የክህሎት ማጎልበቻ ማኑዋሎችን ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በማዘጋጀት እንዲሁም የግንዘቤና የክህሎት ትምህርቱን ከመስጠት አኳያ የእያንዳንዱ ባለድርሻ ሚና ምን መሆን አለበት?

### 6.7. የካርቦን ንግድ ኤክፐርቶች ማፍራት በሚመለከት፣

የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት የማዘጋጀት አገራዊ አቅማችን ገና ማደግ አለበት:: ስለዚህ በዚህ መስክ የማማከርና ፕሮጀክት የማዘጋጀት እንዲሁም ገለልተኛ የቁጥጥርና ማረጋገጫ በመስጠት የስራ መስክ የሚሰማሩ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች መፈጠር አለባቸው:: ይህ ሲሆን የንፁህ የልማት ዘዴ ፕሮጀክት አዘጋጅቶ ለማስተግበር የሚያስፈልግ አጠቃላይ ወጪ ይቀንሳል:: አለባለዚያ ለየፕሮጀክቱ ከውጭ ባለሙያ እየመጣ የሚሰራ ከሆነ የፕሮጀክቱ ማዘጋጃና የማስተግበሪያ ወጪ ከፍ ይላል:: በከፍታውም ልክ ወደ አገር የሚመጣ ኢንቨስትመንት ይደክማል::

## 7. የመረጃ ምንጭ


A Comparative Analysis (WPS4136, February 2007), at http://econ.worldbank.org/WBSITE/EXTERNAL/EXTDEC/EXRESARCH/O.,Content MDK: 212153 28 ~ Page PK: 641654011piPK:641650261thesitePK: 469382,00,html

CBD Ad HOC Technical Expert Group on Biodiversity and Climate Change (2003) Interlinkages Between Biological Diversity and Climate Change: Advice on the Integration of Biodiversity Considerations into the Implementation of the United Nations Framework Convention on Climate Change and its Kyoto Protocol, CBD Technical Series No.10, Draft Report for Experts and Government Review, CBD Secretariat: Montreal.

Climate Change 2007: Impacts, Adaptation and Vulnerability. Contribution of Working Group II to the Fourth Assessment Report of the Intergovernmental panel on Climate Change, for a discussion of the impacts.

Department for International Development (2002) "Sustainable Livelihoods Guidance Sheets" DFID: London. Internet: http://www.livelihoods.org

Environmental Protection Authority of Ethiopia, Justification Submitted for the Ratification of the Kyoto Protocol.

GTZ, Capacity Development for the CDM, Lessons Learned in Ghana, India, Indonesia, South Africa and Tunisia.

Martin Khor, Development Issues Crucial for Post-2012 Climate Regime (TWN Briefing Paper 40, September 2007) at www.twnside.org.sg

Matthew Stilwell, An Economic Sector Approach to Climate Negotiations, Institute for Governance and Sustainable Development (October 2007)

Oxfam International, Adapting to Climate Change: What's Needed in poor countries and Who should pay (2007), at http://www.oxfam.org/en/policy/briefingpapers/bp104_Climate_Change _0705.

Saphores, J.D. (2003) "Harvesting a Renewable Resource Under Uncertainty" Journal of Economic Dynamics and Control 28: 509-529.

Stockholm Environment Institute (2003) "Community-Scale Adaptation Assessment: Paper presented at first AIACC Regional Workshop and Open Meeting for Africa and Indian Ocean Islands, Hartebeesportdam, Brits, South Africa, 10-13 March 2003.

The Conservation Strategies of Ethiopia, 2 April 1997.

The Environmental Policy of Ethiopia, 2 April 1997.

The Kyoto Protocol to the Convention on Climate Change, Opened for Signature on the 16th of March 1998.

The Nature Conservancy (2001) People Matters: The Nature Conservancy's use of Social Science to Understand and Work within the Human Context of Conservation, The

Nature Conservancy: Arlington.

The Right to Development in a Climate Constrained World (September 2007), at http://www.ecoequity.org/docs/The GDRs Framework. pdf.

The United Nations Framework Convention on Climate Change, 9 May 1999.

The World Bank (2003) What International Investors Look For When Investing in Developing Countries, Energy and Mining Sector Board Discussion paper 6 http://iris37.worldbank.org/domodoc/PRD/Other/PRDDContainer.nsf/All+Documents/85256D2400766CC785256FFC00762921/$File/Investors paper No6.pdf.

UNFCCC (2006) Regional Distribution of Clean Development Mechanism Project Activities, http://cdm.unfcc.in/EB/027/eb27_repan19.pdf.

UNFCCC Secretariat, Report on the Analysis of Existing and Potential Investment and Financial Flows Relevant to the Development of an Effective and Appropriate Response to Climate Change (Dialogue Working Paper 8, 8 August 2007)

## 8. ተጨማሪ መረጃ

**POTENTIAL FOR INVESTMENT**

### 8.1 Hydropower

The exploited percentage is estimated as 3.3%. Ethiopia will continue short of electric power supply unless new plants are built. Given the time to commission a new plant, the current electricity generation system could soon be viewed as vulnerable. About 10% of the economically feasible potential is deemed to be suitable for small-scale.

### 8.2 Solar

The average daily solar radiation reaching the ground varies from 5.55 KW/m2 in February and March to 4.55 KW/m2 in July, with a mean of 5.20 KW/M2. The annual variation is small, allowing for a very efficient use of solar energy facilities. (CSE, Vol. 2)

### 8.3 Wind

Ethiopia has exploitable reserve of 10,000 MW wind energy with an average speed of 3.5–5.5m/s, 6 hours/day. The potential for wind energy is estimated to be some 4.3 million Tcal/year, of which 5% is deemed exploitable. 49.8% of this exploitable potential is located in two regions.

### 8.4 Natural gas

Natural gas deposits of over 25 billion cubic meters are discovered in one region. Geothermal energy resources totaling 700 MW are available in four areas.

### 8.5 Biomass

The total energy that can be derived annually from wood, agricultural residues, animal waste and human excreta are estimated to be about 101,656.77 Tcal. Out of which the share of woody biomass is about 79%, followed by animal waste 11 %t, crop residue 8 % and human excreta 2%. The potential of sink in the forestry sector is immense. Last year alone, more than 750 million trees were planted. In one region, a total of 210,832 hectares of land are reforested through natural regeneration and enrichment plantations. (CSE, Vol. 2)

### 8.6 Bio-fuel/diesel potential

There is considerable potential, without impacting on food security, for the production of bio-fuel from energy crops/trees. The possible annual production of energy from these resources is estimated to be 1, 066 Tcal . The existing Sugar Factories are estimated to produce annually no less than 28 million liters of ethanol from raw molasses. In the coming 5 years the capacity of producing ethanol will be 5 times more than the current production.

### 8.7 Bagasse

Sugar factories have a potential to utilize sugar cane refuse, commonly known as bagasse to generate heat and power to meet their own energy requirement. They can also produce and supply electricity to interconnected or isolated grids.

### 8.8 Municipal waste

Per year not lesser than 180.000 tons of refuse is produced in Addis Ababa alone. There is potential to utilize manure from livestock to capture and use methane gas. Studies indicate that about 28,180 Tcal per year can be obtained from human excreta. From the total dung produced annually about 111,284.42 Tcal of energy can be derived.

**8.9 Transport**

There is a huge potential to substitute fossil fuels with compressed natural gas or with fuels derived from biological resources. There is also potential to introduce electric busses for mass transportation. The transport sector of Ethiopia is eligible to the CDM of the Kyoto Protocol if it involves substituting fossil fuels with hydroelectricity, bio-fuels or compressed natural gas for busses and other vehicles. The measure will also reduce dependence on imported fossil fuel and improve the national balance of payment. Availing facilities to run electric busses, creation of a new gas industry, expansion of hydropower electricity and increased production and processing of bio-fuels will result in the creation of employment. Furthermore, it will address other environmental problems like urban air pollution which is an emerging national concern.

**8.10 Organic Agriculture**

Crops produced with the use of compost are proved to be better in terms of coping higher temperature and drought. Organic soils hold more carbon than soils farmed with conventional methods. Conversion of farmers to organic production using compost would enable to store carbon in the soil which will be equivalent to taking about many vehicles off the road in Ethiopia.

# New arrivals

- Ethiopian Journal of Economics Vol. XIV No. 2, Vol. XV No. 1 & No.2 and Vol. XVI No.1
- Quarterly Macro Economic Reports Vol. 6 No. 2
- Proceedings of the Fifth International Conference on the Ethiopian Economy (3 volumes)
- Focus on WTO Vol. 10 No. 4
- Quarterly Macro Economic Reports Vol. 6 No. 3

# CLIMATE CHANGE AND CARBON TRADING IN ETHIOPIA

ATO DESSALEGN MESFIN

## 1. General

Climate change is inherent in nature. It has done repeatedly before, ever since the human species came into being. The Earth's climate system is adaptive. It has the capacity to respond to external forcing such as greenhouse gases and renders them harmless. This capacity has enabled the atmosphere to adapt itself to new phenomena and endure as long as it has. It does not, however, have the capacity to provide immediate response to the change caused to it by such emissions. It takes quite a long time for it to reach the stage whereby it can adapt to the unintended results of climate change. . The current climate change we are experiencing is unique. Even if emission of greenhouse gases into the atmosphere immediately and completely stoped , the global warming we are experiencing now will continue for quite a long time to come. The reason for this is that human interference has the disruptive effect of speeding up the natural rhythm of climate change. Measures to combat impacts of climate change started only when its adverse effects proliferated to reach global proportion. Similarly, the efforts now being made will only pay-off after long years of collective effort. The negative effects of climate change have now assumed a trans-generational dimension.

The Earth's atmosphere has been polluted by the misguided path of development adopted by the developed countries. As a result of pollutants emitted or released into the atmosphere far beyond its capacity, its composition and adaptive power has been disrupted. Because of this, the space for developing countries to trail the path taken by the developed countries to attain their level of development has grown only slimmer. We are not in a position to develop and advance, as the wealthy countries have been doing, by releasing pollutants into the atmosphere. The reason for this is that the ecosystem of the atmosphere, which allows it to absorb pollutants and render them harmless, has been disrupted by the long accumulation of the polluting gases released into it ever since the advent of the Industrial Revolution. This incapacity of the atmosphere to absorb pollutants has resulted in so much

Mr. Dessalegne Mesfin obtained his Masters Degree on Environment for Development in 2007. He also graduated from the Law Faculty of Addis Ababa University and obtained LLB. Previously, he worked as Head of the Legal and Certification Service of the then called Ethiopian Authority for Standardization and served as Public Prosecutor on matters dealing with Metrology. Currently, He is Deputy Director General of the Ethiopian Environmental Protection Authority. He has written and presented numerous studies in the area of environment and development. Representing the country, he has also participated in the various internationally established committees as chair person and member.

congestion that it can no longer accommodate any additional emission. It has thus transpired that to follow the path the developed countries took and attempt to repeat the big historical mistakes they made and hope to succeed in the bargain is simply futile as it is nil.

**2. The Concerns of Different Groups Regarding Climate Change**

The concerns or worries of the world's petroleum producing countries are, first of all, that petroleum emits air polluting-gases. Yet, if petroleum production was to be prohibited, or alternative sources of energy to replace petroleum, were to be developed for use, it would be to their detriment, since petroleum constitutes the foundation of their economy and survival.

The concern of the developed countries, on the other hand, has to do with the possible prohibition of undertaking social and economic development activities that result in the emission of greenhouse gases. The reason for their worries along this line is that, to switch, at this point, to pollution-free development systems and schemes would mean incurring exorbitant expenditure. This in turn would mean that their production and service industries would come to a standstill.

This does not take into account the count of greenhouse gases emitted by the developing countries, which adds to the current climate change around the globe. The fact is that, the climate change the world is experiencing at present poses a bigger threat to those poor people and their environments whose survival directly depends on natural resources; whose infrastructure development is inadequate; and whose social and human capital is poorly developed. The ecosystem's capacity for adaptation is weakened by variations in the climate. As a result of droughts, floods and increased temperature due to climate change, water resources, agriculture, forest vegetations, human habitations, energy supply, human and animal health and other natural and human made resource essential for livelihood and progress will all be damaged. It then stands to reason for us developing countries to insist that we should not be victims of damages whose making we are not part of. It is those who produce and release pollutant gases into the atmosphere that must rectify their mistakes and mend their ways in the first place. The developing countries speak out: it should not be expected of us to halt our efforts to eradicate poverty and to develop in the process in order to absorb the pollutants emitted into the atmosphere by others. Those small islands in the territories of some of the developing countries face the danger of being submerged as a result of the rise in the water levels of oceans and seas. According to the World Bank's estimate, a 1-meter rise in the level of the oceans would

translate into the exposure of 56 million people to risks of being flooded, or drowned. The concern of the people of the developing countries is focused on ensuring the sustainability of their survival. On the other hand, the Scandinavian countries and the Europeans share the concerns of the developing countries and the small islands around the world. They also have an unwavering position on the issue of mitigating or stabilizing the current climate change.

The negotiations on climate change and its effects included these groups of countries

**3. The United Nations Framework Convention on Climate Change**

The United Nations Framework Convention on Climate was adopted in 1992. The Convention is put up together in the nature of a guiding framework. It is not that much different from a policy document. Its contents do not go beyond facilitating the reduction of the emission of pollutants in the atmosphere. According to the Convention, the protection of the atmosphere is an issue of common concern. The disruption of the healthy balance and interaction of the atmospheric ecosystem also is a problem of the same common concern. The primary responsibility for this state of affairs goes to those countries polluting the atmosphere. Climate change is a transboundary. It has negative impacts on all the countries of the world. It has now become evident that increase in the atmospheric temperature disrupts conditions related to the rise of the sea level, the accumulation of snow and rainfall patterns. Unless the emission level of pollutants into the atmosphere is reduced to an acceptable level, water supply will diminish, while food shortage will prevail. The world's biodiversity resources will become vulnerable to extinction. The increase in temperature of the atmosphere will result in the migration of millions of people from their habitat and, in a number of cases, in their demise. It has now become virtually beyond anyone's capacity to contain climate change. Consequently, it has now become quite an imperative for all countries and peoples to learn to adapt to the change. In the developed countries, however, the institutional, technological, and financial capacity to fend off the effects of the current climate change has been developed. Only in the developing countries is such capacity lacking. Any such capacity as possible can be built on the basis of eradicating poverty through development schemes based on the protection of the natural environment. Such an effort as aimed at the eradication of poverty must be of the kind that takes into account the current trend in population growth.

Consequently, in order to undertake development plans in the developing countries that take into account the

efforts now being made to adjust the current trend in the increase of the atmosphere's temperature by 2030, financial resources amounting to USD 200 to 210 billion need to be allotted. USD 28 to 67 billion is needed for building the capacities of developing countries to adapt to the current climate change. According to the estimate of OXFAM, in order to be able to adapt to climate change, the developing countries themselves have to earmark USD 50 billion. The responsibility of covering such expenses, again, goes to the developed countries.

**4. The Negative Impacts of Climate Change on Ethiopia**

It has been articulated in the *Environment Policy of Ethiopia* that, although we are not responsible for the current climate change, it is our national duty to exert moral pressure on those countries that produce pollutants to take the necessary measures to alleviate atmospheric pollution. Droughts have repeatedly inflicted damage on us, as a concomitant consequence of which our fellow countrymen and women numbering in the thousands have been subjected to famine and death. Neither have our rivers and vegetation resources been spared the damage caused by climate change. Not only has the water volume of our rivers diminished, our headwaters themselves have shown signs of desiccation. I may not be able to demonstrate the situation in financial terms, but I can generally say that the negative impact of climate change on Ethiopia has been extreme.

***4.1 The agricultural sector***

Recurrent seasonal disruption, increase in temperature and the protracted duration of the phenomenon have obvious negative impacts on the country's agriculture. Variations in seasonal change, particularly the irregularity of the rainy seasons and its effect on the harvest season, result in reduced crop production. Then droughts set in. To restore the situation to normal or to minimize the effects of the damage requires a considerable stock of wealth. These costs are covered using financial resources that could have been allotted for education, health, road infrastructure, water supply and similar other socio-economic development activities. .

***4.2 The industrial sector***

The damage caused by climate change to water resources, for example, has the ripple effect of weakening the capacity of energy-generating infrastructure. The disruption caused by the weakening of hydroelectric power generation extends from causing shortage in day-to-day consumption to resulting in closure of institutions. To take but one example, those industrial sub-sectors, such as textile factories and tanneries, which largely depend on water for their functional operation, employ a huge human power. In the event that water shortage occurs in such

enterprises, their profit margins will be disrupted. It is obvious, in such circumstances, that lay-offs will follow. This in turn results in the diminution of employment generation and the narrowing of the country's revenue-generation base.

**4.3 Proliferation of disease causing microbes**

Climate variation provides auspicious conditions for malarial infection. Increase in temperature provides the proper condition for the proliferation of disease-causing microbes. The breeding of disease causing microbes and their longevity is very much dependent on heat and humidity. The proliferation or depletion of epidemics varies according to the auspiciousness or otherwise of the environment in which they exist. Water pollution that comes in the aftermath of floods renders people vulnerable to waterborne diseases. In such circumstances, the productive capacities of people with weak health conditions will be compromised. And the expenses incurred in the treatment of diseases and sicknesses will affect the capacity to create assets at the individual, household and country levels.

**4.4 Rangeland degradation**

Pastoralist communities move from place to place in order to satisfy the grazing and water-supply needs of their cattle. The rationale for such movement and change of location is that the location the pastoralists have just vacated will have regenerated itself and be ready to provide goods and services. If, however, the rangeland expected to regenerate itself fails to do so, both the people and their cattle face imminent danger. The effect of this damage is not limited to lack of fodder supply for the cattle. Rather it could go to the extent of causing ruination to the cattle as well as to the communities. The market price of cattle will be disrupted. This disruption in cattle price could have trans-regional impact. If wrangling over limited natural resources occurs, the result could be nothing less than a comprehensive social crisis.

**4.5 Vulnerability of humans to health risks and other hazards**

Floods cause damage to waterworks, sewerage and other infrastructural resources. Hazardous chemicals as well as other disease-causing things could, for example, be washed off from waste disposal depositories or sip into flood waters thereby posing potential hazard to human health. People who have been displaced due to drought or the destruction of their homes by floods stay crowded in the same shelter until they are rehabilitated. When humans, animals, as well as activities, depend on the same limited water resource, the source will be exposed to pollution and become source for waterborne diseases. In such scenarios, before one instance of exposure has been taken care of, another instance of vulnerability could be created. In circumstances like these the damage caused by the second exposure

proves worse than that caused by the first. If, for instance, a person whose residential house has been destroyed by flood counts on repairing his house and hanging out in the flooded area and all this because of lack of alternatives or lack of means and another flood hits the same area, then, the person will sustain more damage than that inflicted by the first flood.

**4.6 Degradation of the state of natural resources**

As a result of flooding and the prevalence of wind due to climatic disorder soils become eroded. The fertility of the soils diminishes, thereby resulting in the weakening of their beneficial capacity. This causes more damage in those parts of our country exposed to desertification. The geographical distribution of such areas in Ethiopia is extensive. The irregularity of rainfall results in water shortage. The biodiversity of water resources diminishes both in quantity and quality, as, for example, the damage inflicted on fish resource as a result of the depletion of water resources. This means that a good majority of the population will be deprived of a cheap, protein-rich food source which the people themselves fish or procure for less.

Climate change causes more damage to lands that are more vulnerable. Water shortage can occur on wetlands as a result of irregularity of rainfall seasons, or due to increase in temperature, which causes loss of moisture through evaporation. The damage caused to wetlands through evaporation means loss of grass for thatching huts, fodder for cattle, breeding ground for birds, including, also, the area's tourist attraction value.

The sustenance of vegetation cover is directly linked to climate change. Just as much as climate change causes damage to the country's biodiversity, so also does the loss of biodiversity cause disruption in climate. Any hazard befalling the environment results in the degradation of the fauna-flora habitat. It is also the case that, because of flooding and increase in temperature, both humans and animals will migrate to other locations. Even if some of them somehow manage to hang on in the affected location, they can only do so at the expense their numbers. On the other hand, it is doubtful those people and animals who happen to inhabit mountainous areas could find suitable locations to which they can migrate.

**5. Clean Development Mechanism**

The United Nations Framework Convention on Climate Change has resolved that, by the year 2000, the developed countries should reduce the amount of emission into the atmosphere by a collective average of 5% below their 1990 levels. But this resolution could not bring the expected result. Consequently, the Kyoto Protocol, which was adopted in 2005, came up with obligatory mechanisms for the

reduction of emission of pollutants into the atmosphere. The Protocol also provides for the responsibility, in this regard, the developed countries should take. The same Protocol encourages developing countries to follow a pollutant-free (clean) development path. Accordingly, the Protocol resolved that the developed countries should reduce their emission by a collective average of 5% from their 1990 baseline over 2008-12. To this effect, the Protocol has proposed three mechanisms; namely, Trade in Emission; Joint (JI) Implementation; and Clean Development Mechanism (CDM). These mechanisms will help polluting companies to reduce their emissions cost effectively. Joint implementation and clean development mechanism require project preparation for their implementation. The geographic areas circumscribed for joint implementation are Eastern Europe and Russia. Clean development mechanism is to be applied in developing countries.

**5.1 Overall institutional setup of clean development mechanism**

